ያቁሙ

# የአየር ወለድ በሽታዎች ንክኪ ቅድሜ ጥንቃቄዎች

**ጎብኚዎች** ከመግባታቸው በፊት ከነርስ ጋር ይገናኛሉ።

## የተከለከሉ ጉብኝቶች

**የክትባት ሁኔታ ወይም የተፈጥሮ በሽታን የመከላከል አቅም ምንም ይሁን ምን ሁሉም የግል መከላከያ መሣሪያዎች ያስፈልጋሉ።**

## ከመግባትዎ በፊት፡



እጅዎን ይታጠቡ



ጋዎንና ጓንት ያድርጉ




National Institute for Occupational Safety and Health(NIOSH,ብሔራዊ የሙያ ደህንነት እና ጤና ተቋም) መተንፈሻ ይጠቀሙ (N95/PAPR/CAPR)

## ሌላ መስፈርቶች፡



**ለአየር ወለድ-በሽታ መከላከያ ክፍል ከፍተኛ ቅድሚያ በመስጠት፣ በር ተከፍቶ እንድቆይ ያድርጉ።**



**ፈሳሽ ነገሮችን ነካክተው ከሆነ፣የዓይን መጠበቂያ፣ የፊት መሸፈኛና መነጽር ይጠቀሙ።**



**ለታካሚ ብቻ የተፈቀዱ ወይም ልጣሉ የሚችሉ መገልገያዎችን ይጠቀሙ። የጋራ መገልገያዎችን በፀረ ተባይ ያጽዱ።**

*ቅድሙ ጥንቃቄ ከተቋረጠና ክፍሉ ከጸዳ በኋላ ምልክቱ Environmental Services (በአከባቢ አገልግሎት) ሠራተኞች እንዲነሳ ይደረጋል።*

Washington State Hospital Association

Washington State Department of HEALTH

7/30/2024

**ከበር ውጪ ያሳዩ። ክፍሉ ንጽህ የአየር ዝውውር እንድያገኝ ሲባል በሩ ለአንድ ሰዓት ዝግ ነው የሚል ምልክት ለጥፈው ይውጡ።**
**ክፍሉ ሙሉ በሙሉ ከጸዳ በኋላ Environmental Services (በአከባቢ አገልግሎት) ሠራተኞች ምልክቱን ያነሳሉ።**

# የአየር ወለድ በሽታዎች ንክኪ ቅድሜ ጥንቃቄዎች

**ሁኔታዎች ላይ በመመስረት የተከለከሉ ጉብኚቶች: ሠራተኞች በመገልገያ ፖሊሲ መሠረት ለጎብኚዎች ተገብውን ትምህርትና የግል መከላከያ መሣሪያዎች(PPE) የግድ መስጠት አለባቸው።**

---

## የግል መከላከያ መሣሪያዎች (PPE)

***በመደበኛ ቅድመ ጥንቃቄዎች መሠረት ለሎች የግል መከላከያ መሣሪያውች በተጨማሪ፣ በመጀመሪያ ገጽ ላይ የተዘረዘሩትን የግል መከላከያ መሣሪያዎች በመያዝ፣ የሚከተሉት ቅደም ተከተሎች ለሁሉም የግል መከላከያ መሣሪያዎች ማሳያዎች ናቸው።***

| *የግል መከላከያ መሣሪያዎች (ልገሳ)*<br><br>*ማድረግ።* | *የግል መከላከያ መሣሪያዎች ማውለቅ*<br>**የተጠቀማችሁት CAPR/PAPR ከሆነ፣ በትክክል ለማውለቅ የአምራች አጠቃቀም መመሪያዎችን ይከተሉ።** |
|---|---|
| • የእጅ ንፅህናን ያከናውኑ።<br>• መከላከያ ጋዎን፣ አስተማማኝ የሆነ ጥምጣም/ከረባት ያድርጉ።<br>• መተንፈሻ ወይም የፊት ጭምብል ማድረግ፣ ተስማሚና በትክክል መግጠማቸውን ማረጋገጥ። አስተማማኝና በትክክል መግጠሙን ያረጋግጡ።<br>• የፊት መሸፈኛ ወይም መነጽር ይጠቀሙ።<br>• ጓንቶችን ያድርጉ። | **1.** ከታካሚ ክፍል ውስጥ ከሆናችሁ፣ እጅን በማይበክል መልኩ ጓንቶችን ያውልቁ።<br>**2.** ጋዎን ያውልቁ - ከረባት/ጥምጣም ይፍቱ፣ ሊጣሉ ለሚችሉ ጋዎኖች ማሰሪያ የሚውል ከሆነ ከረባቱን ይቁረጡ። እያንዳንዱን ክንድ ለማስወገድ አንድ ትከሻን በአንድ ጊዜ በመያዝ ያስወግዱ።ካወለቃችሁ በኃላ በመጠቅለል ትክክለኛ ማስቀመጫ ውስጥ ያስቀምጡ። አሁን ከክፍሉ መውጣት ትችላላችሁ።<br>**3.** ስትወጡ፣ የእጅዎን ንጽሕና (የሚታይ ቆሻሻ፣ የሰገራ ንክኪ ወይም ከቅድመ-ጥንቃቄ መጓደል ንክኪ አጋጥምዎት ከሆነ፣ ሳሙና ውኃ ይጥቀሙ) ያከናውኑ።<br>**4.** የፊት መሸፈኛ/መነጽር ያውልቁ - ተበክሎ ሊሆን ስለሚችል የዓይን መከላከያ መጀመሪያ ክፍል አይንኩ።<br>**5.** መተንፈሻ/የፊት ጭምብል በትክክል በመያዝ ያውልቁ - ተበክሎ ሊሆን ስለምችል የፊት ለፊት ክፍል ከመንካት በመቆጠብ እንዳይበክል አድርገው ተገቢ በሆነ መልኩ ይጣሉ።<br>**6.** የእጅዎን ንፅህና ደጋግመውይጠብቁ። |

**እንደ የሚከተሉት ሁኔታዎች ለመጠቀም**
**(የተቋሙ ፖሊሲ ይመልከቱ)፦**

- በኢንፌክሽን መከላከል በተሰጠ መመርያ መሠረት እየተከሰቱ ያሉ በሽታዎች።
- ባህሪያቶች ኤስ.ኤ.አር.ኤስ (SARS)፣ ኤም.ኢ.አር.ኤስ. (MERS)፣ አዲስ ከፍተኛ በሽታ አምጪ የአቪያን ኢንፍሉዌንዛ፣ የዶሮ ፈንጣጣ፣ ስር የሰደድ ዞስተር ያካትታል።
- የዶሮ ፈንጣጣና ስር የሰደድ ዞስተር ኤች.ሲ.ደብልዩ (HCW) የበሽታ መከላከል አቅም ልፈልግ ይችላል። ሠራተኛ እርግጠኛ ካልሆነ የሕክምና ባለሙያ ልያነጋግር ይችላል።

**የታካሚ ምደባ**

- ታካሚን የግል ክፍል ወስጥ ይመድቡ። በይበልጥ የአየር ወለድ በሽታ መከላከያ ክፍል (AIIR) ይመረጣል። የማይገኝ ከሆነ፣ የተቋሙን መመሪያ ይከተሉ።

**ምግቦችና ዕቃዎች**

- ልዩ ቅድመ ጥንቃቄዎች የሉም። የማዕድ ቤት ዕቃዎች ዕቃ ማጠቢያ ውስጥ ይጠቡ።

**የቆሻሻ እና የአልጋ ልብስ ንጽሕና አጠባበቅ**

- አልጋ ልብስ ከታካሚ ክፍል ውስጥ ያስቀምጡ። ከመጠን በላይ ንክኪና አልጋ ልብስ ማራገፍን ያስወግዱ። ለባዮአዛርድ ቆሻሻ፣ ምድብ ቢ የህክምና ቆሻሻ መመሪያዎችን ይከተሉ።

**ክፍልን ማጽዳት**

- ታካሚው ከወጣ በኃላ በተቋሙ መመሪያ መሠረት ክፍሉ ተገቢ የሆነ የአየር ዝውውር (AIIRs) እንድኖረው ለአንድ ሰዓት በሩን ዘግተው ያቆዩ።
- ከአንድ ሰዓት በኃላ በሆስፒታሉ አሠራር መሠረት የግል መጋረጃ ቅየራን ጨምሮ መደበኛ የጽዳት ሂዴቶች ይካሄዳሉ።

**መሣሪያና አቅርቦቶች**

- ክፍል ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ መሣሪያና አቅርቦቶችን ብቻ ይቀመጡ።
- ለታካሚ ብቻ የተፈቀዱ ወይም ልጣሉ የሚችሉ መገልገያዎችን ይጠቀሙ።
- በተቋሙ ፖሊሲ መሠረት ድጋሚ የሚያገለግሉ መሣሪያ/የታካሚ ክፍል ፀር-ተባይ መርጨትና ማጽዳት።

**ትራንስፖርት**

- የታካሚውን የመውጫ ቅድመ ጥንቃቄ ሁኔታ ለተቀባይ ክፍል ማሳወቅ።
- ታካሚው እጁን መታጠብ አለበት። ታካሚው የቀዶ ጥገና ጭምብል ማድረግ አለበት።
- አጓጓዥ ከታካሚው ክፍል ከመውጣቱ በፊት እጁን መታጠብና የግል መከላከያ መሣሪያ ያወጣል። በመጓጓዣ ጊዜ ቀጥተኛ ግንኙነት የሚጠበቅ ከሆነ ተገቢውን PPE ይልበሱ።
- የትራንስፖርት መኪናን ፀረ-ተባይ በመርጨት ያጽዱ።

**ከበር ውጪ ያሳዩ። ክፍሉ ንጽህ የአየር ዝውውር እንድያገኝ ሲባል በሩ ለአንድ ሰዓት ዝግ ነው የሚል ምልክት ለጥፈው ይውጡ። ክፍሉ ሙሉ በሙሉ ከጸዳ በኋላ Environmental Services (በአከባቢ አገልግሎት) ሠራተኞች ምልክቱን ያነሳሉ።**

***በተቋሙ ፖሊሲ መሠረት ቅድሙ ጥንቃቄ ያቋርጡ፡***

***ቅድሙ ጥንቃቄ ከተቋረጠና ክፍሉ ከጸዳ በኋላ ምልክቱ Environmental Services (በአከባቢ አገልግሎት) ሠራተኞች እንዲነሳ ይደረጋል።***

**420-584  April 2024 Amharic**

ይህን ሰነድ በሌላ ቅርጸት ለማግኘት፣ ወደ 1-800-525-0127 ይደውሉ። መስማት የተሳናቸው ወይም መስማት የሚቸግራቸው ደንበኞች ወደ 711 (Washington Relay) መደወል ወይም ወደ doh.information@doh.wa.gov ኢሜይል ማድረግ ይችላሉ።

Washington State Hospital Association

Washington State Department of HEALTH